11ኛ ዓመት ቁጥር 1
11 th Year No.1

ባህርዳር ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar January

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara**

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 6.75
Unit price

| ማውጫ | **Content** |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም<br>የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራር መወሰኛ አዋጅ | Proclamation No. 119/2005<br>The Revised Proclamation for Defining Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Region Council Members. |

<u>አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም</u>

<u>የተሻሻለውን የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ፣</u>

የክልሉ ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስትና በሕዝቡ የተጣለበትን ኃላፊነት በበለጠ ለመወጣት ይቻለው ዘንድ ከሕገ- መንግስቱ ጋር የተገናዘበና ብቃት ያለው ውስጣዊ አደረጃጀት፣ የተሟላ የአሠራር ስልትና ዝርዝር ሥነ-ሥርዓቶች መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ

<u>Proclamation No, 119/2005</u>

**<u>A Revised Proclamation Issued to Define Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation of the Amhara National Region Council Members</u>**

WHEREAS, it is found necessary to lay down efficient internal organization, complete operational system and rules of enabling the Regional Council to better discharge the responsibilities entrusted on it by the Revised

Constitution of the National Region and the public as well;

በስራ ላይ ያለውን የቋሚ ኮሚቴዎች አወቃቀርና አሠራር መርምሮ የክልሉን መንግስት አካላት አደረጃጀት ባገናዘበ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is found appropriate to examine and thereby amend the existing structure and operation of standing committees of the Regional Council in line with organization of government bodies of the Region;

የምክር ቤቱን አባላት መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም በምክር ቤቱ ውስጥ መቀመጫ ያላቸውን የፖለቲካ ፓርቲ ተጠሪዎች አደረ ጃጀትና ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና አስመልክቶ በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የህዝብ ወኪሎች የሆኑት የምክር ቤቱ አበላት የሚጠበቅባቸው የሥነ-ምግባር ደረጃ ከክልሉ ህገ-መንግስት ድንጋጌዎችና ከፌዴራሉ መንግስት የፓርላማ አሠራር መርሆዎች ጋር የተጣጣመ ሆኖ ዲሞክራሲያዊ ባህርያትን የሚያጐለብትና አንፃራዊ ተጠያቂነት ያለበት ሆኖ እንዲቀረጽና ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49/ንዑስ አንቀጽ 3/1 ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

WHEREAS, it is necessary to particularly stipulate pertaining to rights and duties of members of the Council and organization and role of those party whips which have seats in the Council;

WHEREAS, it is necessary to formulate the ethical standard expected from people's deputies in conformity with the provisions of the National Regional Constitution and operational principles of the Federal parliament and thereby make it public in order to promote democratic attributions and prevail accountability thereof;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Article 49 sub Article 3/1/;issues the following proclamation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**1.** አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የተሻሻለው የምክር ቤት አባላት ስነ-ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም “ ተብሉ ሊጠቀስ ይችላል።

**2.** ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. “ሕገ-መንግስት ማለት ጥቅምት 26 ቀን 1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ -መንግስት ነው።

2. “ምክር ቤት” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ነው።

3. “ኮሚቴ” ማለት አንድን ጉዳይ ለማከናወን እንደየሁኔታው በም/ቤቱ የሚቋቋም አስተባባሪ፣ ቋሚ፣ ንዑስ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው።

## Part One
## General

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as" The Revised Council Members Ethics, Definition of Legislative procedure, Committee Organization and Operation proclamation No.119/2005.”

2. **Definitions**

Unless the Context otherwise requires, in this proclamation:

1. “Constitution” means the Revised Constitution of the Amhara National Region issued on November 5,2001

2. “Council” means the Amhara National Regional Council

3. “Committee” means coordinating standing Sub-or Ad hoc committee established, as the case may

4." ቋሚ ኮሚቴ" ማለት በህግ ተወሰኖ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ዙሪያ በቋሚነት የሚሰራ ሆኖ በህገ-መንግስት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ ¾ መሰረት ምክር ቤቱ የሚያቋቁመው ቋሚ ኮሚቴ ነው።

5. "ጊዜያዊ ኮሚቴ" ማለት አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና ተግባሩ በሌሎች ኮሚቴዎች በቀጥታ ሊከናወን የማይችል ነው ብሎ ሲያምን ምክር ቤቱ የሚያቋቁመው ኮሚቴ ነው።

6. "ንዑስ ኮሚቴ" ማለት ማንኛውም የም/ቤቱ ኮሚቴ ለሥራው ቅልጥፍና እንዲያግዘው ከራሱ አባላት መካከል መርጦ የሚያቋቁመው ኮሚቴ ነው።

7. "አስተባባሪ ኮሚቴ" ማለት የምክር ቤቱን አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣ የቋሚ ኮሚቴዎችን ሰብሳቢዎችንና ፀሃፊዎችን የያዘ አካል ነው።

8." አስረጂ" ማለት እንደ ሁኔታው በምክር ቤቱም ሆነ በኮሚቴዎች ረቂቅ ህግን ወይም እንዲብራራ የተፈለገን አንድ ጉዳይ እንዲያብራራ የሚጠራ ሰው ወይም አካል ነው።

4. “Standing Committee” means the standing committee established pursuant to Article 49 sub –Articles 3(4) of the Constitution to Act perpetually within its legally provided jurisdiction

5. “ Ad-Hoc Committee” mean committee to be established by the Council where there is urgent situation and deems necessary, and when the Council believes such function cannot be specifically undertaken by other committees

6. “Sub Committee” means a committee which any committee of the Council establishes electing from among its own members for the expedition of its activities.

7. “Coordinating Committee” means a body consisting of the speaker and the

council,
chairpersons and secretariats of the
standing committees.

8. “Resource person” means a person or a body invited by the Council or committees to expouad his/her views on a draft law or on required issues.



9. "የመጀመሪያ ንባብ" ማለት ማናቸውም የህግ ረቂቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአፈ-ጉባኤው ቀርቦ ከአስተባባሪ ኮሚቴው አባላት ጋር በመሆን በሰነዱ መሰረታዊ ይዘት ላይ አጠቃላይ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለዝርዝር እይታ ወደ ሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የመምራት ሂደት ነው።

10."ሁለተኛ ንባብ" ማለት ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ ማናቸውም የህግ ረቂቅ በአስተባባሪ ኮሚቴው አማካኝነት ለዝርዝር እይታና ምርመራ ወደ ሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴው ለምክር ቤቱ የሚያቀርበው ሪፖርትና የውሣኔ ሃሣብ ሲሆን በቀረበው የኮሚቴው ሰነድ ላይ የሚደረግን ውይይት ይጨምራል።

9.“ First Reading” means the process of reading and general discussion held on fundamental concepts of a draft law by members of the coordinating committee having been submitted to the Speaker before it gets referred to the pertinent standing committee.

10.“ Second Reading” means the discussion on the recommendation and suggestion of

the concerned standing committee, to which the draft law was referred for further inspection by the coordinating committee subsequent to the first reading and thereby presented to the Council



11. “ሶስተኛ ንባብ” ማለት ከሁለተኛ ንባብ በኋላ በስፋትና በጥልቀት እንዲታይ ምክር ቤቱ ለቋሚ ኮሚቴ የመራው ረቂቅ ሕግ እንደገና ወደ ምክር ቤቱ ተመልሶ የሚደረገው የውይይት ሂደት ነው።

12. “የቴክኒክ እርማት” ማለት ማንኛውም የቋንቋና መሰል ግደፈቶች ማስተካከያ ሲሆን በማናቸውም ረገድ የህጉን ይዘት የማይለወጥ ማሻሻያ ነው።

13.“መንግስታዊ አካላት” ማለት ምክር ቤቱ ወይም ኮሚቴዎቹ በቀጥታ የሚከታተሏቸውና የሚቆጣጠሯቸው ሆነው መንግስት በጀት የሚመድብላቸው ተቋማት ናቸው።

**11**. “ Third Reading” means the discussion of the Council members on the returned draft Legislation, which was earlier referred to the standing committee (s) for further ubsequent to the second reading .

12. “Technical Correction” means rectification of language and language like errors that in no way

14.“የመንግስት ተጠሪዎች” ማለት በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ ወይም ያገኙ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ጣምራ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክር ቤቱ ውስጥ የድርጅታቸውን ወይም የድርጅቶቻቸውን ሥራዎች እንዲያስተ-ባብሩ የሚወክላቸው ወይም የሚወክሏቸውና የምክር ቤት አባል የሆኑ አባሎቻቸው ናቸው።

15. “የዋና ተቃዋሚ  ፓርቲ ተጠሪዎች” ማለት የክልሉን መንግስት  ከመሰረተው ወይም ከመሰረቱት የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ጣምራ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመቀጠል ብዙ መቀመጫዎችን ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ስራዎችን በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲያስተባብሩ የሚወክላቸውን የምክር ቤት አባል የሆኑ የፓርቲው አባሎች ናቸው።

modifies the substance of the given

13.“Government bodies” means bodies that are directly supervised and investigated by the Council or committees, and to whom the government allocates budget.

14. “Government whips” means members of the Council representing the political party or coalition of political parties that have won majority seats in the Council to coordinate activities of their part ( parties)

15.“whips of Main Opposition party” means members of the Council representing the political party who, has majority seats next to the political parties which have formed the Regional Government to coordinate to coordinate activities of their party in the Council

16. " የሁለተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ ተጠሪዎች" ማለት ከዋናው ተቃዋሚ ፓርቲ ቀጥሎ ብዙ መቀመጫዎችን ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ የፓርቲውን ሥራዎች በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲያስተባብሩ የሚወክላቸውና የምክር ቤት አባል የሆኑ የፓርቲ አባሎች ናቸው።

17. "የመንግስት ረቂቅ ህግ" ማለት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ውሣኔ ተደግፎ ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ረቂቅ ህግ ነው።

16. “Whips of Second Opposition party means members of the Council representing the political party, who has majority seat next to the main opposition party, to coordinate activities of their party in the council.

17.“Government Draft Law” means a draft law supported by decision of the Council of the Regional Government and presented the Council.

**18**."ብዙሃን ማህበራት" ማለት በእድሜ በጾታና በሙያ የተደራጁ አባላትን የያዙና ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸው ማህበራት ናቸው።

## ክፍል ሁለት

## ስለም/ቤቱ አደረጃጀት ዋና ዋና ተግባራትና የአሠራር ሥርዓት

3. የምክር ቤቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የምክር ቤቱ አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ. የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ
ለ. የአፈ-ጉባኤው ጽ/ቤት
ሐ. የምክር ቤቱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች
መ. የመንግስትና የፓርቲ ተጠሪዎች /Whips/
ሠ. የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተዘረዘሩትን አካላት ሥልጣንና ተግባር በዚሁ አዋጅ የተደነገገ ሲሆን የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባራት ግን በማቋቋሚያ አዋጁ መሰረት የተወሰነ ስለሆነ በዚህ አዋጅ አልተመለከተም።

18." Civic Association " means Associations legally recognized and Consisting of members organized in age, sex and profession.

## Part Two

## The Structure, Major Duties and Working Procedure of the Council

### 3. General Structure of the Council

**1.** The structure of the Council, pursuant to this proclamation, shall be the following:

a. The General assembly of the Council
b. The office of the Speaker
c. Various committees of the Council
d. Whips of political parties that have seats in the Council.
e. The Secretariat of the Council.

2. The powers and duties of bodies specified under sub-Article 1 of this Article shall be provided in this proclamation. However, the powers and Duties of the secretariat of the Council are not enumerated by this proclamation, as they are covered by the proclamation for its establishment.



3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች አካላትን ሊያቋቁም ይችላል።

3. Noth withstanding the provision of sub-Article 1 of this Article, the Regional Council may establish other bodies when it deems necessary.

4. የምክር ቤቱ አጠቃላይ ተግባራት

ምክር ቤቱ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ከተሰጠው ስልጣን የሚመነጩ ሆነው የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1.ልዩ ልዩ ህጎችንና ደንቦችን ማውጣት፤

## 4. Major Duties of the Council

The Council, deriving its powers from Article 49 of the Constitution, shall have the following major duties and responsibilities:

1. Enact Various laws:

2. ርዕሰ መስተዳድሩንና ሌሎች የክልሉን መንግስታዊ አካላት ለጥያቄ የመጥራትና የሕግ አስፈፃሚውን አካል አሠራር መመርመር፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፣

3. የተለያዩ ሹመቶችን ማጽደቅ ወይም እንደአግባብነቱ መስጠት፤

4. ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን ማደራጀትና ሪፖርታቸውን ማዳመጥ መመሪያዎችን መስጠት ወይም ውሣኔዎችን ማሣለፍ።

**5.** ስለአፈ-ጉባኤውና ምክትል አፈ-ጉባኤው አመራረጥ

1. በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/4/ መሰረት ምክር ቤቱን የሚመራ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ በምክር ቤቱ ይምረጣሉ።

2. Call Head of the Government and other government bodies of the Region for questioning; examine the operations of the Executive Body and take appropriate measures when it deems necessary;

3. Approve the appointment of government officials and give appointment as deemed appropriate;

4. Organize committees necessary for its Functions, hear their reports; and give Guidelines and pass decisions thereon.

2.አፈ-ጉባኤውን ለማስመረጥ በመስራች  ጉባኤው መክፈቻ ላይ በሚገኝ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ተወካይ አማካኝነት 5 አባላትን የያዘ አስመራጭ ኮሚቴ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል፡፡

## 5. Nomination of the Speaker and the Deputy Speaker

1. The Council, in accordance with Article 49 sub-Article 3/4/ of the Constitution, shall elect a Speaker and Deputy Speaker of the Council.

2. An election Committee comprising five candidates shall be elected from among Council members upon presence of a representative from the National Electoral Board during the inaugural meeting to get the Speaker elected from council members.



3. ለአፈ-ጉባኤነት እጩ ሆነው የሚቀርቡት ከ 2 የማይበልጡ የምክር ብት አባላት ይሆናሉ፡፡ እነርሱም የምክር ቤቱን ተሰብሣቢ አባላት 1/3 የድምፅ ድጋፍ ያገኙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

4. የቀረቡት አጩዎች ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜ አፈ-ጉባኤው የሚመረጠው እጅ በማውጣት ሲሆን አብላጫ ድምፅ ያገኘው የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ

3. Candidates presented to be a Speaker shall not be more than two Council members. The candidates shall be supported by one –thirds vote of the council members present in a meeting.

4. When there is more than one candidate, the election of a Speaker shall be by raising

ቢኖርም አንድ ተወዳዳሪ ብቻ በእጩነት በቀረበ ጊዜ ምክር ቤቱ በቀጥታ ድጋፍ /አክላሜሽን/ አፈ-ጉባኤውን ይመርጣል።

6. አፈ-ጉባኤውን አስመልክቶ ከዚህ በላይ የተገ ሽ ት ድንጋጌዎች ለምክትል አፈ-ጉባኤውም አመራረጥ በተመሣሣይ ይሰራባቸዋል።

hands, and then a candidate who has got majority vote of the council shall be the Speaker.

5. Notwithstanding the provision of sub-Article 4 of this Article, the Council shall elect the Speaker by acclamation when only one candidate is forwarded.

6. Provisions stated here of concerning the election the Speaker shall also apply for election of the Deputy Speaker.



**6.የአፈ-ጉባኤው ስልጣንና ተግባር**

አፈ-ጉባኤው በህገ-መንግስቱና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

**6.Powers and Duties of the Speaker**

The Speaker, pursuant to the Constitution and this proclamation, shall have the following powers and

| | |
|---|---|
| | duties |
| 1. የም/ቤቱን ስብሰባዎች፣ይመራል፣ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመቀናጀት ዕለተዊ አጀንዳዎችን ይቀርጻል አስቀድሞሞ ለም/ቤቱ አባላት እንዲታወቁ ያደርጋል፣ | 1.Preside over the Council sessions and set agenda in collaboration with the concerned bodies and thereby notify same to members of the Council in advance; |
| 2. ም/ቤቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፣ | 2.Represent the Council in all its relations with third parties; |
| 3. የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ሰብሣቢዎች፣ ፀሃፊዎችና አባላት፣የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንዲሁም ሌሎች በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት የሚሾሙ አካላትን አቅርቦ ያስመርጣል፣ ያሾማል። | 3.Cause election and appointment of chairpersons, secretaries and members of committees of the Council, present& get appointed by the council Head of the Secretariat as well as other bodies; |
| 4. የኮሚቴዎችን ሥራዎች ያስተባብራል፣ | 4.Coordinate the activities of the Committees; |
| 5. የምክር ቤቱን ጽ/ቤት ያደራጃል ጠቅላላ የአስተዳደር ስራዎችን በበላይነት ይመራል፣ | 5.Organize the secretariat of the Council and oversee general administrative activities; |

6. ምክር ቤቱ በአባሎች ላይ እንዲወስድ የወሰነውን የዲስ Ý ሊን እርምጃ ያስፈጽማል።

7. ከሥልጣንና ተግባሩ ውስጥ በከፊል ለምክትል አፈ-ጉባኤው በጽሁፍ ሊሰጥ ይችላል፣

8. በም/ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**7. የምክትል አፈ-ጉባኤው ስልጣንና ተግባር**

ምክትል አፈ-ጉባኤው ተጠሪነት ለአፈ-ጉባኤውና ለምክር ቤቱ ሆኖ በህገ-መንግስቱና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

6. Cause execution of disciplinary measures decided by the council against its members;

7. May delegate part of his powers and duties to the Deputy Speaker in writing;

8. Undertake such other activities as may be assigned to him by the council;

**7. Powers and Duties of the Deputy Speaker**

The Deputy Speaker being accountable to the Speaker and the Council shall have the following powers and duties pursuant to the Constitution and this proclamation:

1. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ወይም አቋም ይዞ በምክር ቤቱ ውይይት ለመሳተፍ በሚፈልግበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል፡፡

2. በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**8.** የምክር ቤቱ የስብሰባ አይነቶች፤ ምልዓተ-ጉባኤና የውሣኔ አሠጣጥ ሥርዓት

1. ምክር ቤቱ የሚከተሉት የስብሰባ አይነቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ. መደበኛ ስብሰባ
   ለ. አስቸኳይ ስብሰባ

2. በህገ-መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ/በአዋጅ ቁጥር 112/1997 ዓ.ም/እንደተሻሻለ መሰረት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ የምክር ቤቱ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡ ውሣኔዎች በስብሰባው በተገኙ የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይተላለፋሉ፡፡

**9**. ህግጋትና ደንቦችን የማውጣት ስነ-ስርዓት

1. ምክር ቤቱ ህግ የሚያወጣው አዳዲስ ህግጋትን በመደንገግ፣ ነባር ህግጋትን በማሻሻል ወይም በመሻርና የተለያዩ ወሣኔዎችን በማሣለፍ ይሆናል፡፡

1. Represent the Speaker in his absence or when he is unable to carry out his functions or when he wants to participate in the discussion of the council siding to his own stand;

2. Undertake such other functions as may be especifically assigned to him by the speaker

**8.Type of Meeting, Quorum and Decision Making Procedure of the Council.**

1. The Council shall have the following types of meetings:

   a) Regular Meeting
   b) Extra ordinary Meeting

2. Where more than half members of the Council Present at the meeting shall constitute a quorum according to Sub-Article 2 of Article 54 of the Constitution as amended by proclamation No.112/2005; and decisions shall be passed by majority vote of council

members present at the meeting.

## 9. Legislative Procedure

1. The Council shall enact law by promulgating of new statutes, amending or repealing old laws and passing Various decisions.



2.ህግ የማመንጨት ተግባር በዋነኝነት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት አካላት ይኸው ስልጣን አላቸው

ሀ. አፈ-ጉባኤው፣

ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣

ሐ. የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች፣

*2.*As the principal draft law initiator shall be the Council of the Regional Government, the following bodies shall also have the power to initiate draft laws:

a) The Speaker

b) The Regional Supreme court;

c) Committees of the Council*;*

መ. የምክር ቤቱ አባላት፤

ሠ. ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ የሆኑ ሌሎች መንግስታዊ አካላት፣

ረ. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የብሔረሰብ፣የወረዳ ወይም የከተማና የቀበሌ ምክር ቤት

ሰ. የብዙሃን ማህበራት።

3. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥሮች /ለ/እና/ሠ/ የተጠቀሱት አካላት ህግን የሚያመነጩት በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን ዙሪያ ይሆናል።

4. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ስር የተደነገገው ቢኖርም ፋይናንስ ነክ ረቂቅ ህግጋትን የማመንጨት ስልጣን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ብቻ ነው።

5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ ቁጥር /መ/ መሰረት የሚቀረብ የህግ ረቂቅ በጽሁፍ ከተዘጋጀ በኋላ አቅራቢውን ጨምሮ ቢያንስ ሃያ የም/ቤቱ አባላት ፊርማ ተደግፎ

d) Members of the Council;

e) Other government institutions accountable to the Council;

f) Nationality, Woreda or City or Keblee Councils in the Region;

g) Civic associations.

3.The bodies specified in sub-Article 2 (b) and(e) above, may initiate laws within their jurisdiction given to them by law.

4.Notwithstanding to the provision in sub-Article 2 and3 a bove, only the Council of

ለአፈ-ጉባኤው መቅረብ አለበት።

the Regional Government shall initiate financial draft laws.

5.A draft law to be presented in accordance with sub-Article 2 (d) above shall be in writing and supported by at least 20 members of the Council and be submitted to the Speaker.



6.ማናቸውም የህግ ረቂቅ በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ በኩል ለምክር ቤቱ መቅረብ ይኖርበታል።

6.Any draft law shall be submitted to the Council through the Speaker.

**10.**የመጀመሪያ ንባብ

1. አፈ-ጉባኤው በአጀንዳ የተያዘውን የህግ ረቂቅ ይዘቱን በአጭሩ ካቀረበ በኋላ አስተባባሪ ኮሚቴው በህጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች ላይ እንዲወያይ ይደረጋል።

2. ውይይቱ እንደተጠናቀቀ የህግ ረቂቁ በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ቁጥር ተሰጥቶት ወደ ሚመለከተው ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች ይመራል።

## 10. First Reading

1. The Speaker shall breifly present a content of the draft law which is held as agenda, and later he/she causes the coordinating committee deliberate on the detail provisions of the draft law.

2. Upon winding-up of deliberation on the draft law, It shall be numbered and referred to the pertinent committee ( s) through the Speaker.



3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የሚወጣው ሕግ በአስቸኳይነቱ የሚታመንበት ካልሆነ በስተቀር ሕጉ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አጥንቶ የውሣኔ ሃሣቡን ለምክር ቤቱ ለማቅረብ ቢያንስ 15 የሥራ ቀናት ማግኘት ይኖርበታል።

3. The concerned standing committee to which the draft law is referred shall require at least 15 working days to examine the draft legislation and thereby submit its recommendation to the Council, unless the draft law to be issued in applying the

## 11. ሁለተኛ ንባብ

1. አፈ-ጉባኤው ከመጀመሪያ ንባብ በኋላ ለቋሚ ኮሚቴ በተመራ የህግ ረቂቅ ላይ የተዘጋጀው የውሣኔ ሃሣብና አስተያየት በቋሚ ኮሚቴው አማካኝነት ለምክር ቤቱ እንዲነበብ ያደርጋል፡፡

2. አፈ-ጉባኤው በቀረበው የውሣኔ ሃሣብ ላይ ዝርዝር ውይይት በምክር ቤቱ ይካሄድበት ዘንድ መድረክ ይከፍታል፡፡

3. በህግ ረቂቁ ላይ የሚካሄደው ውይይት እንደተጠናቀቀ በሰነዱ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ምክር ቤቱ ያሳልፋል፡፡ ሊጠቃለል ካልቻለ ግን ለተጨማሪ ዕይታ ወደሚመለከተው ኮሚቴ ተመልሶ እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ይመራል፡፡

provision of sub Article 2 of this Article is belived urgent for an immediate enactment.

## 11. Second Reading

1. Subsequent to the first reading, the Speaker Shall cause the standing committee, to which the draft law has been referred, read out the draft proposals and comments it has forwarded on the draft law to the Council.
2. The Speaker shall open a platform for elaborate discussions on the submitted legislation draft proposals.

3. Upon winding –up of the deliberation on the draft law, the Council shall pass final decision. If the deliberation cannot be concluded, the draft law shall be referred to the pertinent committee for further investigation.



## 12. ሶስተኛ ንባብ

## 12. Third Reading

1. ዳግም ጉዳዩ የተመራለት ኮሚቴ የሚሻሻለውን አሻሽሎ የመጨረሻውን የውሣኔ ሃሣብ በማዘጋጀት ለም/ቤቱ በንባብ እንዲያሰማ ይደረጋል፡፡

2. በቀረበው የመጨረሻ የውሣኔ ሃሳብ ላይ ም/ቤቱ በቂ ውይይት በማካሄድ ይወሰናል፡፡

**13.** ሕጉ ስለሚፀድቅበት፣ ስለሚፈረምበትና ስለሚታተምበት ሁኔታ

**1.** አፈ-ጉባኤው የሕግ ረቂቁን ም/ቤቱ መክሮ የተስማማበት መሆኑን በመግለጽ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 3

1. The Committee to which the draft law is re-referred shall be caused to read out the amended version to the Council by preparing its final recmmendations.

2. Subsequent to holding sufficient delibrations on the final draft proposals submitted, the Council shall make decisions thereto.

**13.Ratifing, signing and publishing the law**

1. The Speaker, inaccordance with the power vested in him under sub-Article 3/b/of Article 60 of the Constitution,

ፊደል ተራ ቁጥር ለ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይፈርምበት ዘንድ ለብሔራዊ ክልሉ ኘሬዚዳንት ይልከዋል፡፡

2. Ý ሬዚዳንቱም በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይፈርማል፡፡ በዚሁ የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ ሆኖም ሕጉ በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከመውጣቱ በፊት የቴክኒክ እርማት ማድረግ የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ እርማቱን አፈ-ጉባኤው ያደርጋል፡፡

3. የፀደቀው ህግ በአፈ-ጉባኤው አማካኝነት ቁጥር ተሰጥቶት በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ይታተማል፡፡

4. ሕጉ ከመታተሙ በፊት ከቴክኒክ እርማት ባሻገር መሟላት ያለበት ክፍተት ሲገኝበት በሚመለከተው አካል አማካኝነት ክፍተቱን የሚያሟላ ሃሣብ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ በዚያው ሕግ ላይ ተካቶ ይታተማል፣ ስለተካተተው ሃሣብም ከመታተሙ በፊት የክልሉ Ý ሬዚዳንት እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

Shall send the draft law to the president of the National Region for signitature that the Council has discussed and ratified it.

**2.** The president shall sign a law submitted to him within fifteen days, If, however, The president does not sign the law within this time limit, the legislation shall come in to force. The speaker of the Council may undertake technical correction, Prior to its publication in the Zike Hig Gazette of the Regional State.

**3.** The approved law shall be numbered by the Speaker and there by published in the Zike Hig Gazette of the Regional State.

**4.** When non technical correction are detected before publication of the law, a Suggestion of corrections shall be submitted by the Concerned body and be endorsed by the Council; the suggestion Shall be included in the law and get published; the president of the National Region shall be informed about the suggestion incorporated in the

law before
it gets published.



**14.** መንግስታዊ አካላትን ስለመከታተልና ስለመቆጣጠር

**1.** ምክር ቤቱ የክልሉን መንግስታዊ አካላት የሚከታተልበትና የሚቆጣጠርበት ዋና አላማ፡-

ሀ/ የህዝብና የመንግስት ሃብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን፣

ለ/ ስራዎች ህግና ሥርዓትን መሠረት አድርገው እየተከናወኑ መሆኑን፤

ሐ/ ፍትሃዊና ፈጣን የልማት አቅጣጫ መያዙን

መ/ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትንና መልካም አስተዳደር መስፈኑን፤

ሠ/ የዜጐች መብት፣ሠላምና ደህንነት መከበሩን፣

## 14.Following up and Monitoring State Bodies

5. The main purpose of the Council to follow up and monitor the Regional State bodies shall be whether:

   a) Public and government resources and property are utilized properly;

   b) Activities are being carried out in accordance with rules and regulations;

   c) there exists fair and rapid development dirction;

   d) democracy and good-gover names are prevailing;

   e) citizens rights, peace and security are maintained; and

6. ሪፖርት በኃላፊው ተወካይ ሊቀርብ የሚችለው፣ኃላፊው ሊቀርብ ያልቻለበትን ምክንያትና በተወካዩ የሚቀርብ መሆኑን ለአፈ-ጉበኤው አስቀድሞ በማሣወቅ ብቻ ይሆናል።

7.የም/ቤቱ አባላት በአፈ-ጉባኤው በሚሰጣቸው ቅደም ተከተል መሰረት ለሪፖርት አቅራቢው ጥያቄና አስተያየት ያቀርባሉ።

8.ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ መሰረት ለም/ቤቱ በተሰጡት መልሶች ዙሪያ ተጨማሪ ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲቀርቡ ያደርጋል።

9. ሪፖርቱን አስመልክቶ የማጠቃለያ አስተያየት ይሰጣል፣አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ም/ቤቱ የሚመለከተውን ቋሚ ኮሚቴ ተጨማሪ ማጣራትና ምርመራ አድርጎ ሪፖርት እንዲያቀርብለት ሊያዝ ይችላል።

10.ም/ቤቱ የቀረበውን ሪፖርት አዳምጦ መሰረታዊ ችግር አለበት ብሎ ያመነ

6.Where the report is presented by a representative of the official, the Head of the Office shall make an advance notification of this to the Speaker explaning the reasons for failing to show up presonally.

7.Members of the Council shall, according to the Order given to them by the Speaker, raise questions and forward suggestions to the report prsenter.

8.Additional questions and

እንደሆነ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

comments shall be forwarded on the explanations and answers given in accordance with sub-Article 7 of this Article.

9.Concluding statement about the report shall be given; where necessary, the Council may order that a concerned standing committee make additional investigation and scrutining; and submit areport thereof.

10.Where the Council hears the report presented and believes that the report is with a basic problem, it shall take the necessary measure.



**16.** **የዕለታዊ አጀንዳዎች አቀራረብ**

**1.** ምክር ቤቱ የሚወያይባቸው አጀንዳዎች

## 16. Setting of Agenda

1.The agendas on which the

የሚመነጩት፡-

ሀ. ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት፣

ለ. ከአፈ-ጉባኤው፣

ሐ. ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

መ. ከምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች፣

ሠ. ከምክር ቤት አባላት፣

ረ.ለምክር ቤቱ በቀጥታ ተጠሪ ከሆኑ ሌሎች አካላት፣

ሰ. ከፓርቲ ተጠሪዎች።

Council shall deliberate may emanate from:

a) The Council of the Regional Government

b) The Speaker

c) The Regional Super me Court;

d) Various Committees of the Council;

e) Members of the Council;

f) Other bodies that are directly accountable to the Council;

e) Party whips



**2.** ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ሥር በተጠቀሰው አማካኝነት የሚቀርብ ማናቸውም አጀንዳ ቅድሚያ ተሰጥቶት ውይይት ይደረግበታል።

3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት

2.Any agenda that emanates from the body stated under sub-Article 1/a/above shall get priority for discussion.

የሚመነጩ አጀንዳዎች ለምክር ቤቱ የሚቀርቡት በአፈ-ጉባኤው በኩል ይሆናል፡፡

4. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ማናቸውም የመወያያ አጀንዳ ጉባኤው ከመካሄዱ ከ 1 ወር በፊት ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም ምክር ቤቱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ልንወያይበት ይገባል ተብሎ በአስቸኳይነቱ የታመነበት ማንኛውም ጉዳይ በምክር ቤቱ አካላት ከቀረበና ከግማሽ በላይ በሚሆኑት ድጋፍ ካገኘ በአጀንዳነት ተይዞ ውይይት ሊደረግበት ይችላል፡፡

6. በአጀንዳዎች አቀራረብ ቅደም ተከተልና ለውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ በተመለከተ የመንግስት ዋና ተጠሪ እና አፈ-ጉባኤው በጋራ በመመካከር ይወስናሉ፡፡

**3.** Agendas that are initiated in accordance with sub-Article 1 of this Article shall be presented to the Council through the Speaker.

**4.** Any agenda presented to the Council for deliberation shall be submitted to the Speaker of the Council one month before the Council holds its meeting

**5.** Notwithstanding to the provision provided in under sub-Article 4 of this Article, any issue that the Council belives to be urgent during its meeting may be held as agenda and discussed when it is presented by members of the Council and got the support of more than half of same.

**6.** The government chief whip and the Speaker shall decide together upon priority of agendas and time required for discussion.

**7.** የሌሎች የፓርቲ ዋና ተጠሪዎች እንዲያዙላቸው በሚፈልጓቸው አጀንዳዎችና ለጉዳዩ የሚያስፈልገውን የውይይት የጊዜ መጠን አስመልክቶ ከመንግስት ዋና ተጠሪ ጋር ይመካከራል።

**8.** በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በቀረቡ አጀንዳዎች ምክር ቤቱ በእያንዳንዱ ላይ ድምፅ ይሰጣል። በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍም በአጀንዳነት ይያዛል።

**9.** ምክር ቤቱ በአጀንዳነት ባፀደቃቸው ጉዳዮች ላይ በቂ ውይይት በማድረግ ያሣልፋል።

10. ምክር ቤቱ የተለየ አቅጣጫ ካላስቀመጠ በስተቀር በአንድ ጉባኤ ውድቅ የሆነ አጀንዳ በዚያው ዓመት ተመልሶ ለምክር ቤቱ አይቀርብም።

7. Chief whips of other parties shall consult the government chief whip regarding their proposed agendas and time required to discuss the issue.

8. The Council shall vote on each of the agendas presented pursuant to sub-Article 3 of this Article. The agenda supported by Majority vote of the council shall be deliberated upon.

9. The Council shall pass decisions after adequately delibtating upon the approved agendas.

10. Unless stated by the Council other wise, an agenda rejected at one meeting of the Council shall not come again to the Council in same year.

## ክፍል ሶስት

### ስለምክር ቤት አባላት መብቶችና ግዴታዎች፣ የስነ-ምግባር ሁኔታ፣ስለኮሚቴዎች ውስጣዊ አደረጃጀትና አሠራር

17.ስለምክር ቤቱ አባላት መብቶች፣ግዴታና የሥነ-ምግባር ደረጃ.

የምክር ቤቱ አባላት በሕገ-መንግስቱና በዚህ አዋጅ የተሰጧቸውን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጓቸው መብቶች ሁሉ ይኖሯቸዋል። በአንፃሩም የክልሉ ህዝብ የጣለባቸውን ኃላፊነቶችና የሥነ-ምግባር ግዴታዎች በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል።ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ ይደነገጋል።

**18**. ስለምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች ምክር ቤቱ በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/4/ና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት የኮሚቴ ዓይነቶች ይኖሩታል።

1. አስተባባሪ ኮሚቴ፣
2. ቋሚ ኮሚቴ፣
3. ንዑስ ኮሚቴ፣
4. ጊዜያዊ ኮሚቴ።

## PART THREE

### Rights, Obligations, Rules of Code of Conduct of Members of the Council and Internal Organization and Operation of the Committees

17.**Rights,Obligations and Standard of Rules of Code of Conduct of the Members of the Council**

Members of the Council shall have all rights that are necessary and enable them to exersise powers and duties entrusted to them by the Constitution and this proclamation. They shall properly discharge the responsibilities and rules of code of conduct laid upon them by people of the Region. Particulars shall be determind by a regulation to be issued pursuant to this proclamation.

**18.Various Committees of the Council**

The Council, in accordance with sub-Article 3/4/ of Article 49 of the Constitution and this proclamation,shall Have the following types of committees:

1. Coordinating Committee;
2. Standing Committee;
3. Sub-Committee;
4. Ad-Hoc Committee.



**19. ስለአስተባባሪ ኮሚቴው አደረጃጀት፣ ሥልጣን፣ተግባራትና አሰራር**

**1.** አስተባባሪ ኮሚቴው፡-

ሀ. አፈ-ጉባኤውን፣ምክትል አፈ-ጉባኤውን፣የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሣቢዎችንና ፀሃፊዎችን ወይም ተወካዮቻቸውን በአባልነት የያዘ ነው።

**19. Organization,powers,Duties and Operation of the Coordinating Committee**

**1. The Coodinating Committee shall:**

a) Comprise the Speaker, the Deputy Speaker, chairpersons and secretaries or representatibes of the latter of the standing committees as members;

20. የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት

1. ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡-

ሀ. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

ለ. የአቅም ግንባታና ማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

ሐ. የበጀትና የመንግስት ሂሣብ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

መ. የህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣

ሠ. የሴቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ።

2. ቋሚ ኮሚቴዎቹ ተጠሪነታቸው ለም/ቤቱ ይሆናል።

**20. Organization of the Standing Committe.**

4. The Council,pursuant to this Proclamation,shall have the following standing committees:

a) Economic Affairs standing Committee;

b) Capacity Building and Social Affairs Standing Committee;

c) Budgetary and Government Finance Affairs

d) Legal and Administrative Affairs Standing Committee;and

3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሣቢውንና ፀሃፊውን ጨምሮ በአፈ-ጉባኤው አቅራቢነት በክልሉ ም/ቤት የሚመረጡና ከ 5 እስከ 9 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

4. አንድ የም/ቤት አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ ቋሚ ኮሚቴ በላይ አባል ሆኖ ሊሠራ አይችልም።

e) Women's Affairs Standing committee.

2. The standing committees shall be Accountable to the Council.

3. Each standing committee shall have 5 to 9 members including the chaiperson and the secretary who are elected by the Council upon recommendation by the Speaker

4. Amember of the Council shall not be a member of more than one standing committee at one time.



5. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሣቢዎች ተጠሪነታቸው ለአፈ-ጉባኤውና ለየኮሚቴዎቻቸው ይሆናል።

21. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

1. የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ፣-

ሀ. የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነትን

5. The chairpersons of the standing committees shall be accountable to the Speaker and their respective committees.

21. **Economic Affairs Standing Committee**

1. The main objective for establishing the Economic

እንዲያድግ፣በምግብ እህል ራስን የመቻልና የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ዓላማችን ግብ እንዲመታ

Affairs Standing committee is:

a) To develop product and Productivity of the agricultural econmic sector;achieve the objective of ensuring food self sufficiency and food security:



እንዲሁም ግብርና-መር የሆነው የኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂያችን እንዲሣካ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣Ý ሮግራሞች እቅዶች በተገቢው መንገድ መፈጸማቸውን መከታተልና መመርመር፤እንዲሁም

ለ. የሃገሪቱ ንግድና እንዱስትሪ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት በሚያፋጥን መልኩ ተግባራዊ መሆኑን፣ንግድና ኢንዱስትሪ እንደዚሁም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲስፋፋ የሚያበረታቱ ተግባራት በአግባቡ መከናወናቸውን፣ የኢንቨስትመንት ፖሊሲና ህግ በመስኩ ለሚሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን መፈጠራቸውን ማረጋገጥ ይሆናል።

follw up and examine policies,programmes and work plans issued for the attainment of the agriculture-led economy development strategy are implemented in a proper way.

b) To ensure that the country's Trade and Industry policy and strategy is implemented in manner to expedit the econmic development of the Region;the

proper undertakings of activities that encourage the promotion of trade,industry as well as small and micro enteprises;whether the investment policy and laws create conducive conditions for investors to involve in the sector.

2.የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መንግስታዊ መ/ቤቶች ይከታተላል፡-

ሀ. የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ፣

ለ. የንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፣

ሐ. የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ

መ. ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥሮች ሀእና ለ ስር ለተጠቀሱት ቢሮዎች ተጠሪ የሆኑ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች፡፡

2. The Economic Affairs standing Committe shall follow up Government offices listed here below:

a) Agriculture and Rural Development Bureau;

b) Trade,Industry and Urban Development Bureau;

c) Water Resource Development Bureau,

d) Offices and organizations that are accountable to the bureaux cited under (a) and (b) herein above.



**3**.ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ/2/ድንጋጌ ሥር የተዘረዘሩትን አካላት በተመለከተ በማናቸውም ህጎች ተለይተው በተሰጧቸው ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ ረቂቅ ሕግ አዘጋጅቶ ለም/ቤቱ ያቀርባል፣ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ይመረምራል፡፡

**3**.It shall prepare and shbmit a draft law
to the Council concerning the powers and duties enumerated specifically by any laws to the bodies mentioned in sub-Article 2of thisArticle;monitor,follow

4.የኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ስር የተሰጡትን ኃላፊነቶች በተሻለ አኳኋን ለመወጣት ራሱን በሚመለከት ሁለት ንዑሣን ኮሚቴዎች ከፋፍሎ ስራውን ያከናውናል።

upand,where deemed necessary,examine same thereof.

4.The Economic Affairs Standing Committee,with a view to more Effectivelydischargingitsresponsib ilities specified under sub Articles (2) and (3),shall undertake its activities by Organizing itself in to the following two sub-committees:



ሀ. የግብርናና ገጠር ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ፣

a) Agriculutral and Rural Development Affairs Sub committee;

ለ. የንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ።

5.የግብርና ገጠር ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር ሀ ስር የተመለከተውን ቢሮና ለራሱ ተጠሪ የሆኑትን መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች አሰራር የሚከታተልና የሚመረምር ሲሆን የንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጉዳዮች ንዑስ ኮሚቴ ደግሞ በፊደል ተራ ቁጥር ለ ስር የተመለከተውን ቢሮና ለርሱ ተጠሪ የሆኑትን መንግስታዊ መስሪያቤቶች እንዲሁም በፊደል ተራ ቁጥር ሐ የተመለከተውን ቢሮ አሰራር የመከታተል ኃላፊነት ይኖርበታል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና የተደነገገው ቢኖርም የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች አስመልክቶ የሚዘጋጅ የህግ ረቂቅ ቢኖር ለአፈ-ጉባኤው የሚቀርበው በንዑሣን ኮሚቴዎች ሣይሆን በኢኮኖሚ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ይሆናል።

b) Trade ,Industry and Urban Development Affairs Sub-Committee.

